**መመሪያ ቁጥር 882/2014**
**የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ**

የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና የሚያስከትለው ጉዳት ለመቀነስ ስለሚወሰዱ ክልከላዎች እና ግዴታዎች በተመለከተ ከዚህ በፊት የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 803/13ን አሁን ካለው የወረርሽኙ ነባራዊ ሁኔታ ወረርሽኙ እየቀነሰ መሆኑና ለበሽታው ክትባት መኖርና መንግስት ለማሕበረሰቡ በነጻ እያቀረበ በመሆኑ፣

ሲተገበሩ ከነበሩ የጥንቃቄ እርምጃዎች የተወሰዱ ትምሕርቶች መሰረት በማድረግ በማሕበረሰቡ ላይ ለሚፈጠረው ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ስነ-ልቦናዊ ጫናዎችን የሚቀንሱ እና ውጤታማ በሆኑ የመከላከያ መንገዶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ አዲስ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፡

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በመድኃኒትና ምግብ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 72 ንዑስ-አንቀፅ (2)፣ በምግብ፣ መድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661 አንቀፅ 55 ንዑስ-አንቀፅ (3) እና የምግብ፣ የመደኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀፅ 98 መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 882/2014” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ኮቪድ-19" ማለት በዓለም የጤና ድርጅት በይፋ በዚህ ስም የሚጠራው ተላላፊ በሽታ ነው፡፡
2. ”ኮሮና ቫይረስ” ማለት የኮቪድ-19 በሽታ የሚያመጣ ተህዋስ ማለት ነው፡፡
3. “ስብሰባ” ማለት ማንኛውንም ተግባር ለመፈጸም፣

**Directive No. 882/2022**

**REVISED DIRECTIVE TO PROVIDE FOR THE PREVENTION AND CONTROL OF THE COVID-19 PANDEMIC**

Whereas, it has become necessary to revise the prohibited activities and duties to be imposed on individuals to prevent and mitigate the impact of COVID-19 provided under Directive No 803/2022 based on the current situation of the pandemic and provision of COVID-19 vaccination freely by the government.

WHEREAS, it has become necessary to issue new Directive that will reduce economic, social, and psychological stress on the community and that focus on effective prevention measures by taking lessons from the implementation of the former precautionary measures,

NOW, THEREFORE, this Directive is issued by the Ethiopian Public Health Institute in accordance with Article 72 (2) of the Food and Medicine Administration Proclamation No. 1112/2019, Article 55(3) of the Food, Medicine, and Healthcare Administration and Control Proclamation No. 661/2009, and Article 98 of the Council of Ministers Regulation on Food, Medicine, and Healthcare Administration and Control No. 299/2013.

## 1. Short Title

This Directive may be cited as the “An amended Directive to provide on Prohibited Activities and Imposed Duties for the Prevention and Control of COVID-19 Pandemic No. 882/2022”.

## 2. Definition

In this Directive, unless the context requires otherwise:

1. “COVID-19” means the communicable disease designated as such by the World Health Organization.
2. “Corona virus” means a virus that causes the Covid-19 disease;
3. “Meeting” means the gathering of four or more persons who do not belong to a single family, in an indoor place

ለመነጋገር፣ ስልጠና ለመስጠት፣ ለመወያየት፣ ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣ ወይም መሰል ተግባራትን ለማከናወን የአንድ ቤተሰብ አባላት ከሆኑ ውጪ አራትና ከዚያ በላይ ሆኖ ከሁለት ሰዓት በላይ በቤት ዉስጥ ወይም ድንኳን በመሳሰሉ በተከለለ ሁኔታ በአካል መገኘት ማለት ሲሆን እንደ አግባብነቱ እንደ ሠርግ፣ ምርቃት፣ እና መሰል የማህበራዊ ዝግጅቶች ለማድረግ የሚደረግ መሰባሰብም ያጠቃልላል፡፡

4. "ዲፕሎማት" ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ደረጃ አላቸው ተብሎ የተረጋገጠላቸው ሰዎች ማለት ነው፤

5. “ከስደት ተመላሽ” ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ከኢትዮጵያ ወጥቶ በስደት የኖረና በራሱ ፈቃድ ወይንም በመንግሥት ስምምነት ያለ ፓስፖርት ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ወይም በተቀባዩ አገር የጥገኝነት ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ እና በራሱ ፈቃድ በሌሴ-ፓሴ ወይም በነበረበት አገር መንግሥት ተገዶ ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ነው፣

6. “RT PCR” ማለት በሞለኪዉላር ቴክኒክ የኮቪድ-19 ቫይረስ ምርመራ ስርዓት ነው፡፡

7. “Antigen-Based RDT” ማለት ፈጣን የኮቪድ-19 የምርመራ ዓይነት ነው፡፡

8. ”ራስን በራስ መመርመር” ማለት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም አንቲጂንን መሰረት ያደረገ የ“Antigen-Based RDT” እራስን በራስ ፈጣን የኮቪድ-19 ምርመራ ነው፤

9. “የኮቪድ-19 ምልክቶች” ማለት በኮቪድ-19 የተያዘ ሰው ላይ ሊስተዋሉ የሚችሉ እንደ ትኩሳት፣ የራስ ምታት፣ የሳል፣ ጣዕምና ሽታን መለየት አለመቻል፣ የጉሮሮ አካባቢ ቁስለቶች እና የመሳሰሉ ምልክቶች ናቸው፡፡

10. “ኮቪድ-19 ፖዘቲቭ” ማለት በRT PCR ወይም ሌሎች ቫይረሱ በሰውነት ውስጥ መኖሩን ሊያሳዩ በሚችሉ የምርመራ ዓይነቶች ቫይረሱ እንዳለበት የተረጋገጠ ሰው ማለት ነው፡፡

for the purpose of collectively carrying out any activity, discussion, or any similar purposes and includes social events such as weddings, graduations and similar activities as the case may be.

4. “Diplomat” means those persons recognized by the Ministry of foreign affairs as having diplomatic status.

5. “Returnee” means any Ethiopian who left Ethiopia for any reason as a refugee and is in the process of returning to the territory of Ethiopia on his own or per a government's agreement without a passport, or any Ethiopian whose asylum petition is denied by the receiving country and is in the process of returning to the territory of Ethiopia on his own wish or compelled to be deported by the government of his temporary residence with a *Laissez-passer*;

6. “RT PCR” means a laboratory diagnosis of COVID-19 through molecular techniques;

7. “Antigen-Based RDT” refers to a Rapid Diagnostic Test for COVID-19 which is an accelerated laboratory diagnosis procedure;

8. “Self-test” means Antigen-based rapid diagnostic test which can be performed by the patient at any place or time to rapidly identify COIVD-19 test result.

9. “COVID-19 symptoms” means any symptoms manifested by a person with COVID-19 including fever, headache, cough, loss of taste and smell, throat pain, and similar other symptoms;

10. “COVID-19 positive “means any person whose COVID-19 infection is confirmed through RT PCR, or other similar other laboratory diagnosis method to detect the presence of the virus in the human body;

11. “ኮቪድ-19 ኔጌቲቭ” ማለት በRT PCR ወይም ሌሎች ቫይረሱን በሰውነት ውስጥ መኖሩን ሊያሳዩ በሚችሉ የምርመራ ዓይነቶች ቫይረሱ እንደሌለበት የተረጋገጠ ሰው ማለት ነው፡፡

12. “ከኮቪድ-19 ማገገም” ማለት እንደ ታካሚው ሁኔታ ጊዜን ፣ የኮቪድ-19 ምልክት ሁኔታን ወይም የኮቪድ-19 ምርመራን መሰረት በማድረግ በጤና ባለሙያ የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ታካሚው ምልክት የሌለው ከሆነ ምርመራ ካደረገበት ቀን አንስቶ በሚቆጠሩ 07 ተከታታይ ቀናት ወይም ታካሚው ምልክት የሚያሳይ ከሆነ ምልክት ከጀመረበት ቀን አንስቶ በትንሹ 07 ቀናትና ተጨማሪ ከምልክት ነጻ የሆኑ 3 ቀናት በኋላ ይሆናል፡፡

13. “ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች” ማለት ለኮቪድ-19 እና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች የበለጠ ተጋላጭ የሚሆኑ በማረሚያ ቤቶች ፤ በስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች ፤ በተፈናቃይ ማቆያ ጣቢያዎች ፤ በአረጋዉያን መጦሪያ ሥፍራዎች፣ በማገገምያና የአእምሮ ህክምና ማዕከላት እና የመሳሰሉት ቦታዎች ውስጥ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡

14. “ጸረ ተሕዋሲያን ውህድ” ማለት ከኮሮና ቫይረስ ወይም ሌሎች በሽታ አምጭ ተሕዋስያን ጋር ንክኪ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ እቃዎችን ለማጽዳት የሚውል ከአልኮል ወይም ከክሎሪን/በረኪና የተዘጋጀ ውህድ ማለት ነው፡፡

15. ”የመግቢያና መዉጫ ኬላ” ማለት ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ፣በድንበር የሚገኝ መቆጣጠሪያ ኬላ ፣ ሥልጣን ባለው አካል የተሰየመ ደረቅ ወደብ ነው፡፡

16. ”የተሟላ ክትባት ” ማለት የመጨረሻው ክትባት ከተወሰደ በኋላ ሁለት ሳምንት የሞላው እና እንደየክትባቱ አይነት አስትራዜኒካ፣ ሲኖፋርም፣ ሲኖቫክ፣ ሞደርና እና ፋይዘር ክትባቶችን ሁለት ጊዜ እና ጆንሰን ጆንሰን ክትባት አንድ ጊዜ መዉሰድ ነው፤

17. “ቤተሰብ” ማለት በአንድ ቤት ውስጥ በአንድ ላይ የሚኖሩትን አባላት ማለት ነው፣

11. “COVID-19 negative “means the absence of a detectable level of coronavirus within the human body and is confirmed through RT PCR, or other similar laboratory diagnosis methods to detect the presence of the virus in the human body;

12. “Recovery” refers to declaration of an individual free from COVID-19 which is decided according to the health professional on time based, symptom based and test based criterions. If a patient is asymptomatic he will be declared recovered 7 days after the day of sample collection for RT-PCR test which turned positive or the day of positive Ag-RDT test. If a patient is symptomatic he will be declared recovered after minimum of 7 days from the date of start of symptoms and additional 3 days without symptoms.

13. “Congregate setting residents” means Sections of the community which are prone to COVID-19 and other infectious transmissible diseases because of living in high risk areas like prisons, internally displaced people sites, refugee camps, elderly homes and others.

14. “Disinfectants” means alcohol or chlorine-based compound and is intended to disinfect articles or materials supposed to harbor coronavirus or other disease causing organisms;

15. “Point of entries” means international airports, land borders and dry ports designated by an appropriate authority.

16. “Full vaccination” means 2 weeks after taking of the single dose for Johnson and Johnson, and 2 doses for AstraZeneca, Sinopharm, Sinovac, Moderna, and Pfizer.

17. “Family” means household members who live in a house;

18. ”ተቋም” ማለት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ማንኛዉም በግል፣ በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት የሚተዳደር ህጋዊ ዕውቅና ያለው ተቋም ነው፡፡

19. በወንድ ፆታ የተገለጹት አነጋገሮች የሴትንም ፆታ ያካትታሉ፣

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመላ አገሪቱ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል::

## 4. የተከለከሉ ተግባራት እና ግዴታዎች

1. ማንኛውም ኮቪድ-19 እንዳለበት የተረጋገጠ ሰው ቫይረሱ እንዳለበት እያወቀ ወደ አገር ውስጥ መግባት፣ ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል ወይም ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ በሚችልበት ሁኔታ ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘት የተከለከለ ነው፤

2. ማንኛውም የኮቪድ-19 ምልክቶች የታየበት ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ በአግባቡ የማድረግ ፣ ራስን በራስ በፈጣን የኮቪድ-19 ምርመራ የማድረግ ወይም በጤና ተቋም ምርመራ በማድረግ ዉጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነ ለሚመለከተው አካል በፕሮቶኮሉ መሠረት ሪፖርት እና ክትትል የማድረግ እንዲሁም አጠቃላይ የኮቪድ-19 መከላከያ ተግባራትን የመፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡

3. ማንኛውም የኮቪድ-19 ፖዘቲቭ የሆነ ሰው እንደህመሙ ክብደት የጤና ባለሙያ በሚወስነው አግባብ ከበሽታው እስኪያገግም ድረስ በቤቱ ውስጥ ወይም በጤና ተቋም እራሱን ለይቶ የማቆየት ሃላፊነት አለበት፡፡

4. ማንኛውም ተቋም ወይም ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው አገልግሎቱን በሚሰጥበት ጊዜ ሰራተኛው እና ተገልጋዩ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ የማድረግ እና የማስደረግ፣ በርና መስኮት ክፍት የማስደረግ በቂ የአየር ዝዉዉር እንዲኖር የማድረግ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ተቋሙ የንፅህና መጠበቂያ እንደ ሳሙና እና ዉሃ ወይም ሳኒታዘይርም የማዘጋጅትም ግዴታ አለበት፡፡

18. “Institution” means any governmental, non-governmental or privately owned organization that is legally recognized.

19. Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of application

The Directive shall be applicable to all efforts to be done in Ethiopia to prevent and control the COVID-19 pandemic.

## 4. General Prohibited Activities and Duties Imposed

1. It is prohibited for any person who knows he is infected with coronavirus to enter the country, mix with the general public or meet with people in any situation that may allow the virus to spread;

2. Any person showing COVID-19 symptoms has the duty to appropriately wear face mask, get self-test or test at health facility and follow as well as implement general COVID-19 preventive measures if tests positive.

3. Any COVID-19 positive person shall isolate himself either at home or health facility according to the severity of the illness until declared recovered by a health professional.

4. In any institution including transportation service providers, the employee and customers thereof shall appropriately wear face mask and the institution to ensure employee and customers appropriately wear face mask, adequate ventilation by opening doors and windows and personal hygiene materials like soap, water and hand sanitizer is provided.

5. ከሚሰጡት የአገልግሎት አይነት ከተገልጋይ ጋር ፊት ለፊት የሚገናኙ በመሆኑ ለኮቪድ-19 ስርጭት ተጋላጭ የሆኑ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንደ ጤና ተቋማት ፣ ባንኮች ፣ ሆቴሎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ፣ህግ አስከባሪ ተቋማት እና የመሳሰሉት ተቋማት ሰራተኞቻቸው የተሟላ የኮቪድ-19 ክትባት እንዲወስዱ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

6. ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ያሉባቸው ተቋማት ሰራተኞቻቸው የተሟላ የኮቪድ-19 ክትባት እንዲወስዱ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

7. ማንኛውም የግልም ሆነ የመንግሥት ትምህርት ቤት ፣ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የፊት ለፊት ትምህርት ሲሰጥ ትምህርት የሚሰጥበትን ሁኔታ ወይም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሥራውን በተመለከተ በዚህ መመሪያ እና በሌሎች አግባብነት ባለቸው መመሪያዎች የሚወጡ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር ወይም ሌሎች ዝርዝር የትምህርት አሰጣጥ ስታንዳርዶችን ሳይከተል ትምህርት መስጠት የተከለከለ ነው::

8. በጤና ተቋም ውስጥ በኮቪድ-19 የሚከሰት ሞት ጤና ተቋሙ አስክሬኑን በጥንቃቄ አስተካክሎና አሽጎ ለሟች ቅርብ ቤተሰብ ማስረከብና ሟች በማዕከሉ ሲገለገልባቸው የነበሩ የግል ቁሶች በጸረ-ተህዋሲያን ውህድ በማጽዳት ለቤተሰብ የማስረከብ እና ሌሎች በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡

9. የአረጋዉያን መጦሪያ ሥፍራዎች፣ የማገገሚያና የአእምሮ ህክምና ማዕከላት ሰዎችን በአካል ለመጠየቅ የኮቪድ-19 ክትባት የተከተቡ መሆን አለባቸው ካልሆነ በአግባቡ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ በማድረግ መጠየቅ አለባቸው፡፡

## 5. በመግቢያ እና መዉጫ ኬላ ስለሚደረግ የጤና ቁጥጥር

1. ማንኛዉም ከአስር አመት ዕድሜ በላይ የሆነ በመግብያ መዉጫ ኬላ የሚገባ ተጓዥ መንገደኛ ከመነሻው ሀገር ከመነሳቱ በፊት 72 ሰዓት ወይም ሶስት ቀን በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ የRT PCR ምርመራ ኔጌቲቭ ውጤት ወይም 24

5. Service providers, such as health facilities, banks, hotels, transport providers, law enforcement agencies and the like that are vulnerable to COVD -19 transmissions due to their frontline nature to communicate face to face with customers and have the responsibility to get their employees fully vaccinated against COVID-19.

6. Congregate setting Institutions are responsible to get their staff fully vaccinated against COVID-19.

7. It is prohibited for any public or private school, for any public or private college or university to provide face to face education without respecting the directives that shall be enacted regarding precautionary measures in methods of education delivery or the general teaching and learning process or other detailed standards of education delivery;

8. Health facilities where the death occurred have a duty to clean with disinfectants the materials used for the deceased, return the materials to the family, and perform activities provided in manual prepared at the national level.

9. To physically visit elderly care centers, psychiatry and rehabilitation centers, it is mandatory to be fully vaccinated against COVID-19 or appropriately wear face mask at all times during the visit.

## 5. Border and Point of entry controls

1. Any international traveler above the age of ten coming through international airports of the country shall bring a certificate of negative RT PCR test done up to 72 hours or three days before departure or Ag-RDT negative test up to 24 hrs. before arriving to Ethiopia.

ሰዓት ወይም አንድ ቀን በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ የAntigen RDT ምርመራ ኔጌቲቭ ውጤት ይዞ መምጣት አለበት።

2. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 እንዳለ ሆኖ መንገደኛዉ በ90 ቀን ውስጥ በኮቪድ-19 ታሞ ያገገመ ከሆነ ወይም የተሟላ የኮቪድ-19 ክትባት ያጠናቀቀ ከሆነ እና ለዚሁ ማስረጃ ካቀረበ ያለ ምርመራ ወደ አገር መግባት ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 ቢኖርም በአገሪቱ የዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በኩል የሚገባ የትራንዚት መንገደኛ አየር መንገዱን ወይም አየር መንገዱ ከለያቸው ሆቴሎች ለቆ ወደ ከተማ የማይገባ ከሆነ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ተፈፃሚ አይሆንበትም ሆኖም አየር መንገዱ ወይም አየር መንገዱን ከለየው ሆቴል ለቆ ወደ ከተማ የሚገባ ከሆነ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 ተፈፃሚ ይሆናል ወይም በአየር መንገዱ ወይም በተለየው ሆቴል የኮቪድ ምርመር ተደረጎለት ኔጌቲቭ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን ይህን የማስፈፀመም ኃላፊነትም የአየር መንገዱ ይሆናል፤፤

4. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 ቢኖርም መንገደኛዉ ዲፕሎማት ከሆነ እና በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላ ከሆነ በአየር መንገዱ ወስጥ የኮቪድ 19 ምርምራ ተደርጎለት ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገባ የሚደረግ ሲሆን የምርመራ ዉጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነ ወይም ለምርመራው ፍቃደኛ ካልሆኑ ግን እራሱን ለ 7 ቀናት ለይቶ የማቆየት ኃላፊነት ይኖርበታል።

5. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 ቢኖርም መንገደኛዉ ከስደት ተመላሽ ከሆነ እና የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ድንጋጌዎች የማያሟላ ከሆነ በአየር መንገዱ ውስጥ የኮቪድ 19 ምርምራ ተደርጎለት ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገባ የሚደረግ ሲሆን በምርመራ ውጤት መሰረት የኮቪድ 19 ታማሚ መሆኑ ከተረጋገጠ ኢኒስቲትዩቱ ባዘጋጀው ፕሮቶኮል መሰረት ክትትል የሚደረግበት ይሆናል፡፡

6. ማንኛዉም በመግቢያ እና መዉጫ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ይዞት

2. Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this Article, the traveler shall enter the country if he has a certificate of recovery from COVID-19 within 90 days or if he has completed the COVID-19 vaccine in full and provides evidence;

3. Without prejudice to sub article 1 and 2 of this article, if transit passenger entering through international airports of the country do not enter the city or do not leave his hotel designated by the airline, sub article 1 and 2 of this article doesn’t apply on him Whereas if he is to enter the city leaving the airline or hotel designated by the air-lines, sub article 1 and 2 shall apply or shall be tested negative with Ag-RDT done at the airlines or hotels des-ignated by the airlines.

4. Notwithstanding the provisions of sub-article 1 and 2 of this Article, if the traveler is a diplomat and fails to ful-fill the requirements provided under sub-article 1 and 2 of this article, he shall be tested at the airport and enter the country. Whereas if the test result is positive or if he refuses for test, he shall self-isolate for 7 days,

5. Notwithstanding the provisions of sub-article 1 and 2 of this Article, a returnee may enter the country by taking Ag-RDT test at the airport if he does not fulfill the re-quirements provided under sub article 1 and 2 of this ar-ticle. If the test result is positive, he shall be followed up in accordance with the relevant protocol,

6. Any person providing transport services at point of en-tries has the duty to ensure that provisions of this article

ለሚገባ መንገደኛ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት አለበት

7. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ቢኖሩም ድንበር አቋራጭ ተሽከርካሪዎችን የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎችና ረዳቶች እና የኢትዮ-ጂቡቲ የባቡር ትራንስፖርት አሽከርካሪዎችና ረዳቶች የትራንስፖርት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 6. በስብሰባ ወቅት መወሰድ ስላለባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

1. ማንኛውም የስብሰባ ተሳታፊ በስብሰባው ወቅት በአግባቡ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሲሆን የስብሰባው አዘጋጅም ይህን የመከታተልና የማስተግበር ኃላፊነት አለበት፡፡

2. ስብሰባው የሚጠራው አካል ስብሰባው በሚጠራበት ጊዜም ይሁን በስብሰባ ወቅት የስብሰባው አዳራሽ በቂ የአየር ዝውውር ያለው መሆኑን የማረጋገጥ እና በስብሰባ ወቅት በቂ የአየር ዝዉዉር እንዲኖራቸው የማድረግ፣ የእጅ ንጽህናን ለመጠበቅ የሚያስችሉ በቂ ግብዓቶችን የማዘጋጀት ወይም የተዘጋጀ መሆኑ የማረጋገጥ፣ ተሰብሳቢዎች የሚጠቀሙባቸው እና በተደጋጋሚ በእጅ ሊነካኩ የሚችሉ ቁሳቁሶችን በየጊዜው በጸረ-ተህዋሲያን ውህድ የማፅዳት ወይም እንዲፀዱ የማድረግ ፣ እና ሌሎች ለዚህ ተብሎ በወጣ ማንዋል የተዘረዘሩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመተግበር እና እንዲተገበሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 7. ስፖርታዊ ውድድሮች በተመለከተ

1. ማንኛውም ስፖርታዊ ውድድር ለማካሄድ የስፖርታዊ ዉድድሩ አዘጋጆች እና ተወዳዳሪዎች የተሟላ የኮቪድ-19 ክትባትን የወሰዱ መሆን ያለባቸው ሲሆን ይህን የማያሟሉ ከሆነ ግን ከውድድሩ ጊዜ በፊት ከ24 ሰዓት ወይም ከአንድ ቀን በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ ኔጌቲቭ የAntigen RDT ምርመራ ውጤት ወይንም ከ72 ሰዓት ወይም ከሶስት ቀን በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ ኔጌቲቭ የRT PCR የምርመራ ውጤት ይዘው መምጣት አለባቸው፡፡

are applied.

7. Notwithstanding the provisions of this article, drivers of cross-national vehicles and captains of trains and their co-drivers and co-captains shall be governed by a directive issued by the Ministry of Transport.

## 6. Precautionary Measures that Shall Be Taken during Meetings

1. Any meeting attendee is obligated to appropriately wear face mask and meeting organizer shall ensure the implementation.

2. Making sure the meeting hall has sufficient air ventilation, preparing sufficient materials useful for keeping hand hygiene, as much as possible separating the entrance and the exit, cleaning materials the participants use and repeatedly touch with disinfectant at least twice a day, and taking other precautionary measures provided in the manual.

## 7. Precautionary measures that shall be taken during sport tournament

1. To conduct any sporting event, the organizers and competitors of the sport must have received a complete Covid-19 vaccine or shall have a certified negative Ag-RDT negative test result done no more than 24 hours or negative RT PCR test result done no more than 72 hours or three days.

2. Hosts and organizers of any sports tournaments shall conduct the tournament by fully implementing appli-

2. የማንኛዉም ስፖርታዊ ውድድር አዘጋጆች የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ማንዋሎች መሰረት የሚወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመተግበርና የማስተግበር ኃላፊነት አለባቸው።

3. እነዚህ ውድድሮች ወረርሽኙን ባገናዘበ መልኩ መከናወን መቻላቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ የመስጠት እና በውድድር ወቅቶችም የጥንቃቄ እርምጃዎቹ የማይተገበሩ ከሆነ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አግባብ ባላቸው የመንግሥት አካላት የሚፈጸም ይሆናል።

**8. ስለግብረ-ሀይል መቋቋም**

የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19 በሽታ) የመከላከልና የመቆጣጠር ስራን በማእከልነት የሚያስተባብር ብሄራዊ ግብረ ኃይል (ከዚህ በኋላ ግብረ ኃይሉ እየተባለ የሚጠራ) በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

**9. ስለግብረ ሀይሉ ሰብሳቢ፣ ስለአባላቱና የአሰራር ስርአት**

1. የግብረ ኃይሉ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል

ሀ/ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር…………..ሰብሳቢ

ለ/ የጤና ሚኒስቴር……………….አባልና ጸሃፊ

ሐ/ የሰላም ሚኒስቴር…………………..….አባል

መ/ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር…………..አባል

ሠ/ የትምህርት ሚኒስቴር……………......አባል

ረ/ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር…አባል

ሰ/ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር……አባል

ሸ/ የቱሪዝም ሚኒስቴር…….……..…አባል

ቀ/ የፍትሕ ሚኒስቴር……………....አባል

በ/ የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር…… አባል

cable cautionary measures stated in sub article 1 of this article and other relevant protocols.

3. The relevant government organs shall be responsible for granting a permit for the conduct of such tournaments with consideration of the pandemic, as well as to take the necessary measures during non-compliance with applicable measures.

**8. Establishment of Task force**

The National Task Force (hereinafter referred to as the "Task Force") hereby established by this Directive as the center for coordination in the prevention and control of COVID-19 pandemic.

**9. Chairman of the Task force, its members and working procedures**

**1. The Task Force shall be accountable to the Prime Minister and shall have the following members**

a. Deputy Prime Minister …………………Chairman

b. Ministry of Health……………Member and secretariat

c. Ministry of Peace ……………………………Member

d. Ministry of culture and sport ……………….Member

e. Ministry of Education ……..……………….Member

f. Ministry of Transport and Logistics…… …...Member

g. Ministry of Trade and regional integration ……Member

h. Ministry of Tourism………………………….member

i. Ministry of Justice - …………………… Member

j. Minister of women and Social Affairs ……...Member

ተ/ የብሄራዊ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን- አባል

ቸ/ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን……………..……..አባል

ኀ/ የጠቅላይ ሚኒስቴር ፕሬስ ሰክሬታሪያት…………..አባል

ነ/ የኢትዮጲያ ሕብረተሰብ ጤና ኢነስቲትዩት……..አባል

2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የተዘረዘሩት አባላት በተቋሙ የበላይ አመራር ይወከላሉ

3. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የግብረ ኃይሉ ሰብሳቢ ሌሎች አካላት የግብረ ኃይሉ አባል እንዲሆኑ ሊወስን ይችላል

4. ግብረ ኃይሉ፣ የስበሰባ የጊዜ ሰሌዳ፣ የድምጽ አሰጣጥና ሌሎች የግብረ ኃይሉ የአሰራር ስርአትን በሚመለከት በሚያወጣው የአሰራር መመሪያ ይወስናል፤

5. የጤና ሚኒስቴር የግብረ ኃይሉ ሴክሬታርያት በመሆን የግበረ ኃይሉ የአስተዳደርና የዕለታዊ ስራዎች ያከናዉናል፡፡

## 10. የግብረ ኃይሉ ስልጣንና ተግባር

በሌላ ሕግ ለሌሎች አካላት የተሰጠዉን ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ግብረ ኃይሉ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

1) የበሽታው ስጋት ከግምት ዉስጥ በማስገባት የተለያዩ የጥንቃቄ እርምጃዎች ተግባራዊ የሚሆንበት የአሰራር ስርዓት በየጊዜው እንዲወጣ አቅጣጫ የሰጣል፣

2) በሳይንስ ተቀባይነት ያገኙት የበሽታዎች የመከላከል ዘዴዎች የሆኑትን እጅ መታጠብን፣ የአፍና የአፍንጫ ጭምብሎችን፣ በእጅ እና ሌሎች በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን እርምጃዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ያበረታታል፣

3) ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልግ የጥናትና ሌሎች ግብአቶች

k. National Disaster and Risk Management Commission – Member

l. Federal Police Commission ………………….Member

m. Press Secretariat of the Prime Minister -……..Member

n. Ethiopian Public Health Institute ……………Member

2. The members listed under sub article 1 of this article shall be represented by their respective heads of the executive organs.

3. Subject to the provisions of sub-article 1 of this article, the Chairman of the Task Force may decide that other bodies shall be members of the Task Force.

4. The Task Force shall decide on the schedule of meetings, voting and other procedures of the Task Force.

5. The Ministry of Health shall be the Secretariat of the Task Force and shall carry out the administrative and daily activities of the Task Force.

## 10. Powers and duties of the task force

Notwithstanding the powers and duties given by other laws, The Task Force shall have the following powers and duties;

1. Giving direction on issuing of periodic guidelines on the procedures for various precautionary measures, taking into consideration the prevalence of the disease;

2. Promoting and enforcing implementation of scientifically proven techniques for the prevention of spread the disease such as hand washing, respiratory hygiene, masks, no hand shaking, and other measures prescribed by this Directive;

3. Consult on the basis of research and other resources re-

መሰረት በማድረግ ምክክር ያደርጋል፣ የአሰራር ስርዓት እና ፖሊሲ በማዉጣት ተግባራዊ ያደርጋል፣

4) በዚህ መመሪያና በሌሎች የአሰራር ስርዓቶች በሚወሰኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እርምጅዎች የሚፈጠር ችግር ለመቋቋም የሚያስፈልግ አመራር ይሰጣል፣

5) በዚህ መመሪያና በሌሎች ይህን መመሪያ ለማስፈፀም በሚወጡ መመሪያዎች ወይም ማንዋሎች የሚወሰኑ እርምጃዎች እና ክልከላዎች አጠቃላይ ተግባራዊነት ያስተባብራል፣

6) ይህን መመሪያ ለማስፈፀም የሚያግዝ ቴክኒካዊ እገዛ ያደርጋል፣

7) አግባብነት ካላቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት በማስተባበር ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

8) አስፈላጊ ሲሆን ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ከዓለም የጤና ድረጅት፣ ከማንኛዉም የመንግስት አካል፣ አለማቀፋዊ ወይም አህጉራዊ ድርጅት በትብብር ይሰራል፣

9) ይህን መመሪያ ተግባራዊ የሚያደርግ የፖሊሲ አቅጣጫ ይሰጣል፣

10) የስጋት ትንተና በማድረግ የበሽታዉን የመከላከልና የሚያስከተለው ጉዳት ለመቀነስ እቅድ ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ እቅዱ በየጊዜው ይከልሳል፣

11) የበሽታው ስርጭት ለመከላከል በሚሰራ ስራ በክልሎችና በተቋሞች የመተባበርና የመቀናጅት ስራ እንዲኖር ያደርጋል፣ ያረጋግጣል

12) የክልሎች የበሽታው የመከላከል ስራ ያስተባብራል፣ አስፈላጊ እገዛ ያደርጋል

13) ለበሽታው ዝግጁነትና ምላሽ (የመከላከል) ስራ የሚያስፈልግ ፋይናንስና የሰው ኃይል ያንቀሳቅሳል፣

14) ስራውን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ንዑስ ግብረ ሀይሎችን ያቋቁማል፣ ስራቸውን

quired for the implementation of this Directive, and implement policies and procedures;

4. Provides the necessary guidance to deal with the problems caused by social and economic measures determined by this Directive and other procedures;

5. Coordinates the general implementation of the actions and prohibitions determined by this Directive and other directives or manuals to implement this Directive.

6. Provides technical assistance in implementing this Directive;

7. Implement this Directive in collaboration with relevant governmental and non-governmental organizations.

8. Cooperate with the World Health Organization, any governmental, international or regional organization to implement this Directive when necessary.

9. Provides policy direction that implements this Directive

10. Develop, implement, and revise plans regularly to reduce the risk and impact of the disease by making risk analysis

11. Encourage and coordinate cooperation between regions and institutions in preventing the spread of the disease.

12. Ensure collaboration and coordination between the national and sub-national level and across sectors;

13. Mobilize the necessary financial and human resources for the preparation and response of the disease;

14. Establishes, monitors and directs various sub-task forces

ይከታተላል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣

15) ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**11. የክልል የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19 በሽታ) መከላከል ግብረ ኃይል**

1) በክልሉ ምክትል ርእሰ መስተዳደር ሰብሳቢነት የሚመራ ከተለያዩ አግባብነት ካለቸው ተቋማት የተዉጣጣ ከብሔራዊ ግብረ ኃይሉ ተቀናጅቶ የሚሰራ የክልል የኮሮና ቫይረስ መከላከል ግብረ ኃይል በየክልሎቹ እንዲቋቋም ይደረጋል።

2) የክልል ግብረ ኃይል ስልጣንና ተግባር እንዲሁም የአሰራር ስርዓት ክልሉ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

**12. የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19 በሽታ) መከላከል ንዑሳን ግብረ ሀይሎች**

በፌዴራልና በየክልሎቹ ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ባሉ የመንግስት መዋቅሮች የተለያዩ ንዑሳን ግብረ ሀይሎች ይደረጃሉ፣ አሰራራቸው ግብረ ኃይሉ በሚያወጣው የአሰራር መመሪያ ይወሰናል፡፡

**13. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

1. ማንኛውም ሰው እና ተቋም ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት።

2. ማንኛዉም ተቋም ሰራተኞቹ የኮቪድ-19 ክትባት እንዲወስዱ የማበረታታት እና ለዚሁም ሁኔታዎች የማመቻቸት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን እንደዚሁም የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በተቋሙ በሚገባ መተግበራቸዉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

3. የሕግ ተጠያቂነት

ሀ/ ይህን መመሪያ በማስፈፀም ረገድ በዘርፉ የሚመለከተው የመንግስት አካል በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች የተላለፈ ሰው ላይ አስፈላጊዉን አስተዳደራዊ እርምጃዎች የመውሰድ እና ለዚህም የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

ለ/ የዚህ አንቀፅን ንዑስ አንቀፅ 4/ሀ እንዳለ ሆኖ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም

to make the work effective

15. Performs other activities to assist in the implementation of this Directive.

**11. Regional Coronavirus (Covid-19 Disease) Prevention Task Force**

1. States' Coronavirus Prevention Task Force will be established in each of the states under the chairmanship of the deputy chief of the state.

2. The powers and functions of the State Task Force as well as the operating system shall be determined by the directive issued by the state

**12. Sub-Task forces for the Prevention of Coronavirus (Covid-19 Disease)**

At the federal and state levels, various sub-task forces shall be organized in state structures from state to kebele, and their operation is determined by the task force's guidelines.

**13. Miscellaneous Provisions**

1. Every person and institutions shall have the duty to cooperate for the implementation of this Directive.

2. All institutions in the country shall have the obligation to advocate and facilitate for the vaccination of their staffs they shall be responsible for the implementation and enforcement of this Directive in their institutions.

3. Legal liability

A. In the implementation of this Directive, the relevant government body shall take the necessary administrative measures against the person who violates the prohibitions and obligations set forth in this Directive and shall establish procedures for this.

B. Without prejudice to sub article 1 of this article,

ሰው አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ አንቀጽ መሰረት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

4. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው መመሪያዎች

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጣር ስለሚወሰዱ ክልከላዎች እና ስለሚጣሉ ግዴታዎች ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 803/ 2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል

5. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 23 ቀን 2014 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት**

**ዋና ዳይሬክተር**

any person who contravenes the restrictions and duties provided in this Directive shall be held accountable as per the relevant provisions of the Criminal Code.

4. Inapplicable directives

A Directive on Prohibited Activities and Imposed Duties for the Prevention and Control of COVID-19 Pandemic No. 803/2020 is hereby repealed.

5. Effectiveness of the Directive

This directive shall come into effect on March 31 /2022 and all stakeholders are mandated for the implementation.

**Addis Ababa, March 31 /2022**

**Director-General**

**Ethiopian Public Health Institute**